# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*
(አንድነት/United)


መጋቢት ፳፪ ቀን ፪ ሺ ህ ፰ ዓ. ም
March 31, 2016

## አፈናና ግድያው ይቁም!

በአፈናና ግድያ የተካነው የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) አገዛዝ ዛሬም በወልቃይት ጠገዴና በዳንሻ ሕዝብ ላይ ዘግናኝ የጭካኔ በትሩን ዘርግቷል፤ አረመኔያዊ ተግባሩን አጧጡፎ ቀጥሏል። የወልቃይት ሕዝብ የማንነት ጥያቄ አስተባባሪ አባል የሆኑት አቶ ሊላይ ብርሃኔ ከጎንደር ከተማ ወደ ዳንሻ ሲጓዙ በህወሓት ታጣቂዎች ታፍነው በመወሰዳቸው ሕዝቡ ልጃችንን የት እንዳደረሳችሁት? አሳውቁን የሚል ጥያቄ ማንሳቱ እንደ ድፍረት ተቆጥሮበት፣ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ በህወሓት ሚሊሻዎችና ፈጥኖደራሾች ብዙ ወገኖቻችን ተደብድበዋል፤ በዳንሻ፣ በሰሮቃና በወልቃይት ዙሪያ የሚገኙ ቤቶችም ተዘርፈዋል፤ በተጨማሪም፣ በህወሓት ልዩ ትዕዛዝ በርካታ ቤቶች እንዲፈርሱ ተደርገዋል። የሚታፈኑትና የሚገደሉት ሰዎች ቁጥርም ከቀን ወደቀን እየጨመረ መሄዱን ከአካባቢው የሚገኘው መረጃ ያስረዳል። ከአቶ ሊላይ መታፈን አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ በጎንደር ከተማ ነዋሪ የነበሩትና የወልቃይቱ ተወላጅ፣ የወልቃይት የማንነት ጥያቄ ጠንካራ ደጋፊ ስለነበሩ በመርዝ መገደላቸውን ተከትሎ የተገኘው መረጃ እንዳሳየው አገዳደላቸው በአገዛዙ በተቀነባበረ ሤራ መሆኑን ያረጋግጣል። ስለዚህ በወልቃይት ጠገዴ፣ ሁመራና ዳንሻ ሕዝብ ላይ ከበፊቱ የበለጠ የከፋ አደጋ አሁንም እያንዣበበ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል።

ከዛሬ 25 ዓመት በፊት የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ድርጅት በጉልበት የጎንደር አካል የሆነውን የወልቃይት ጠገዴንና የሁመራን እንዲሁም የጠለምትን መሬት ወደ ትግራይ በመከለሉ ሕዝቡ እኛ ጎንዴሬ እንጂ ትግሬ አይደለንም፤ ከጥንት ጀምሮ፤ ማንነታችን ጎንደሬ፤ አስተዳደራችን ጎንደር እንጂ መቀሌ ሆኖ አያውቅም በማለት ጥያቄ ያቀረቡ የወልቃይት ጠገዴ፤ እንዲሁም የጠለምት ተወላጆች ተጨፍጭፈዋል፤ ታሥረዋል፤ አካባቢያቸውን ጥለው እንዲሰደዱም ተገደዋል። ከተሰደዱበት አገር ከሱዳን ሳይቀር በሱዳን የፀጥታ ክፍል ተባባሪነት እጅግ በርካታ የወልቃይት ተወላጆች ታፍነው ተወስደው


P.O.Box 91384
Los Angeles, CA 90009

Phone: 202- 241 2078
eprp_united@eprp-ihapa.com

እስካሁኗ ሰዓት ድረስ የት እንደደረሱ ለቤተሰብና ለወዳጅ ዘመድ ግልጽ አይደለም። ይሁን እንጇ ሕዝቡ “ማንነታችን ይከበር” በማለት በተለያዩ መንገዶች ለመብቱና ለማንነቱ መታገሉን አላቋረጠም። ካለፈው ዓመት ጀምሮ ሕዝቡ በወኪሎቹ አማካይነት "ሕገ-መንግሥት" ተብዬው በሚፈቅደው መሠረት በሰላማዊ መንገድ የመብትና የማንነት ጥያቄውን አቅርቧል። የሕዝብን ጥያቄ እንደጦር የሚፈራው የህወሓት አሸባሪ ቡድን በሰላም የተጠየቀን ጥያቄ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ከመመልስ ይልቅ ሰላማዊ ሰዎችን ማፈኑንና ማሳደዱን ቀጥሎበታል። ይህን ሁሉ ስንመለከት፣ መብቱንና ማንነቱን በጠየቀ ሕዝብ ላይ ሃያ አምስት ዓመት ሙሉ ጭካኔ የተሞላበት አፈናና ግድያ ማካሄድ የአምባገነንነት ሥነ-ባህሪን የሚያረጋግጥ መሆኑ ግልጽ ነው። ህወሓት ወልቃይት ጠገዴን፣ ሁመራንና ጠለምትን የሚፈልገው ሕዝቡን ሳይሆን ለም መሬቱን መሆኑን በቅርቡ በትግርኛ በተጻፈው የሚስጥር ሰነድ ውስጥ ይፋ ሆኗል። ሃያ አምስት ዓመት ሙሉ በአካባቢው ተወላጆች ላይ ሲወስድ የኖረው የጭካኔ እርምጃና አካባቢውን በግዳጅ እየለቀቁ እንዲሰደዱ የማድረጉ ዘዴም ይህንኑ የተስፋፊነት ዓላማውን ተግባራዊ የማድረግ ምኞቱን የሚያመለክት ነው። በዚህ የሚስጥር ሰነድ ውስጥ በዝርዝር የተቀመጠው ህወሓት ከዚህ በፊት ሲጠቀምበት የነበረውን የሕዝቡን ማንነት፣ ባህሉንና ቋንቋውን የማጥፋት ዘዴ በረቀቀና በተጠናከረ መንገድ እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርግ ነው።

“አያድን ጋሻ ጎን ያሰብራል” እንዲሉ፣ ጎንደር አካባቢን እያስተዳደክኩ ነው የሚለው አካል በጎንደር ተወላጆች ላይ የህወሓት ጦር ግፍ ሲፈጽም ዝም ብሎ መመልከቱ፣ ለህወሓት ተባባሪነቱን ግልፅ አድርጎ የሚያሳይ ነው። ማንነታችን ይከበር፣ እኛ ዝርያችንም አመጣጣችንም ጎንደሬዎች ነን እያሉ ለሚጮሁ የጎንደር ተወላጆች አገዛዙ ቢያንስ ጉዳዩ በሰላማዊ መንገድ የሚታይበትን መንገድ ማመቻቸት ሲገባው፣ በአድርባይነትና በፍርሃት ተንጦ ለአባይ ወልዱ ታዛዥ በመሆን ሕዝብ እያስጨረሰ ነው።

የትግራይ ሕዝብ ሆይ! በስምህ የሚነግደው የህወሓት ቡድን ከጥቂት የጥቅም ተካፋዮቹ በስተቀር ለአንተ ለሰፊው የትግራይ ሕዝብ የቆመ እንዳይመስልህ! በህወሓት ቅስቀሳ ተሳስተህ በዚህ የአፈናና የግድያ እርምጃ ውስጥ ከገባህ ታሪካዊ ስህተት ይሆናልና ለረዥም ዘመን በሰላምም ሆነ በችግር ጊዜ አብሮህ የኖረውን የወልቃይት ጠገዴን ሕዝብ በአንተ ስም በሚምለውና በሚገዘተው ህወሓት ለዘመናት አብረኸው በኖርከው ሕዝብ ላይ ግፍና

መከራ ሲያደርስበት ከጎኑ ልትቆም ይገባሃል። አገዛዙ ጊዜያዊ ሲሆን፣ የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ግን እንደጥንቱ አብሮህ የሚኖር የችግርህና የደስታህ ተካፋይ ወገንህ ነው። የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ሕዝቤ፣ የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ወገኔ ነው ብለህ መነሳት ይገባሃል! ተነስ! ህወሓት የወልቃይት ጠገዴንና የጠለምትን መሬት የትግራይ ነው ብሎ ከመከለሉ በፊት በእርሻም ሆነ በንግድ ድንበር ሳይገድብህ አብረህ ስትኖር እንደነበር አይዘነጋም። የሁመራ፤ የአብደራፊ፤ የመተማ፤ የወልቃይት መዘጋ የእርሻ ቦታዎች የጎንደሬው ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያውያን በጋራ አርሰው ሲጠቀሙበት እንደነበር የቅርብ ትዝታ ነው። ጎንደሬን አጥፍቶ መሬቱን የትግራይ ማድረግ ታሪክ ይቅር የማይለው ስህተት ስለሆነ ከህወሓት ጎን አትቁም!

የህወሓት ግፍና ጭካኔ መሠረቱ የታላቋ ትግራይ ሪፐብሊክን ከመመሥረት ቅዠት ጋር የተያያዘ ነው። ዛሬ በኦሮሞ፣ በኮንሶ፣ በመተከል፣ በጋምቤላና በሌሎች አካባቢዎች በሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን የጭካኔ ብትር የአንድን ዘር የበላይነት በዘላቂነት ለማረጋገጥ ካላቸው ህልም ጋርም የተያያዘ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (አንድነት) አሁን በህወሓት የተያዘው አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ሕዝብን ከሕዝብ አባልቶ አገሪቱን ሊያፈርስ እንደሚችል ጥርጣሬ የለውም። ስለዚህ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እኩልነትና ለዴሞክራሲያዊ አንድነት የምንታገል የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ተቋማት በተለይም የትግራይ ምሁራን በዚህ ወሳኝ ወቅት በአንድነት ቆመን አገራችንና ሕዝባችን መታደግ ይገባናል። ለዘመናት የታገልንለትና አሁንም የምንታገልለት ዓላማ ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር የፖለቲካ ድርጅቶች ልዩነቶቻቸውን አቻችለው የመከራ ገፈት ቀማሽ ከሆነውን ሕዝባችን ጎን ቆሞ መታገልን ይጠይቃል። ኃይላችንን አስተባበረን ህወሓትን አስወግደን በምንወዳት አገራችን ውስጥ ሰላምና መረጋጋት ሰፍኖ ሕዝቦቿ ከእርስ በርስ ጦርነት ይልቅ በፍቅር፣ በሰላምና በአንድነት ተሳስረው፣ የቁሳቁስም ሆነ የዕውቀት ሀብታቸውን በጋራ ለኅብረተሰብ ዕድገትና ለአገር ብልጽግና እንዲያውሉት ከጎናቸው የመሰለፍ አስፈላጊነት ለነገ የማይባልና ሊውል ሊያድር የማይገባው አስቸኳይ አገራዊ ጥሪ ነው።

በአንድነት ቆመን አገራችንን እንታደግ!

**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **eprp_united@eprp-ihapa.com**